**Global Storybooks**

globalstorybooks.net

ትንሽ ዘር፣ የዋንጋሪ ማታይ ታሪክ

Nicola Rijsdijk
Maya Marshak
Mezemir Girma

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 4.0 International License.
https://creativecommons.org/licenses/by/4.0

# ትንሽ ዘር፣ የዋንጋሪ ማታይ ታሪክ





Nicola Rijsdijk
Maya Marshak
Mezemir Girma

3

አማርኛ am



በምስራቅ አፍሪካ በሚገኘው የኬንያ ተራራ
በአንድ በኩል በሚገኝ አንድ መንደር አንዲት
ትንሽ ልጅ ከእናቷ ጋር በማሳ ላይ ትሰራ ነበር።
ስሟም ዋንጋሪ ይባላል።



ዋንጋሪ ውጪ ውጪውን ማለት ትወዳለች። በቤተሰቧ የአትክልት ስፍራ አፈሩን በገጀራ ትቆፍራለች። ትናንሽ ዘሮችንም ወደ ሞቃቱ መሬት ትከታለች።



ፀሐይ ከገባች በኋላ ያለውን ጊዜ በጣም ትወደዋለች። እጽዋቱ አልታይ ማለት በሚጀምሩበት ጊዜ ዋንጋሪ ወደ ቤቷ መሄጃው ሰዓት መድረሱን ታውቃለች። በማሳዎቹ ውስጥ ያሉትን ጠባብ መንገዶች ተከትላና ስትሄድ እንዳደረገችው ወንዙን አቋርጣ ትመለሳለች።





ዋንጋሪ በ2011 አርፋለች። የሚያምር ዛፍ ባየን ቁጥር ግን ልናስታውሳት ይገባናል።



ዋንጋሪ በጣም ለፍታለች። በዓለም ዙሪያ የነበሩ
ሰዎች ስራዋን አይተው ትልቅ ሽልማት ሰጧት።
የዓለም የኖቤል ሽልማት ይባላል ሽልማቱ።
ዋንጋሪም ይህን ሽልማት ስትቀበል የመጀመሪያዋ
አፍሪካዊት ሴት ነች።





ዋንጋሪ ትምህርት ቤት መሄድ የምትወድ ጎበዝ
ልጅ ነበረች። እናትና አባቷ ግን እቤት ቆይታ
እንድታግዛቸው ይፈልጉ ነበር። ሰባት ዓመት
ሲሆናት ታላቅ ወንድሟ ወላጆቿን ትምህርት ቤት
እንዲያስገቧት አሳመናቸው።



ዋንጋሪም ትምህርት ትወድ ነበር! መጽሐፍ ባነበበች ቁጥር ብዙ እያወቀች መጣች። በትምህርቷ ጥሩ ውጤት ስላስመዘገበች አሜሪካ እንድትማር ተጋበዘች። ዋንጋሪ እጅግ ተደሰተች! ስለ ዓለም ብዙ ለማወቅም ፈለገች።





ከረጅም ጊዜ በኋላም አዳዲሶቹ ዛፎች ደን ሆኑ፤ ወንዞቹም እንደዱሮው መፍሰስ ጀመሩ። የዋንጋሪም መልዕክት በመላው አፍሪካ ተሰራጨ። ዛሬ ከዋንጋሪ ዘሮች ብዙ ዛፎች ተገኝተዋል።



ዋንጋሪ ምን ማድረግ እንዳለባት ታውቅ ነበር። ሴቶቹን ችግኝ እንዴት እንደሚያቸግኑና ዛፍ እንዴት እንደሚተክሉ አስተማረቻቸው። ሴቶቹም ዛፎቹን እየሸጡ ቤተሰባቸውን ማስተዳደር ቻሉ። ሴቶቹ በጣም ተደሰቱ። ዋንጋሪ አቅም እንዳላቸው እንደዲገነዘቡ ረድታቸዋለች።





በአሜሪካውም ዩኒቨርሲቲ ዋንጋሪ ብዙ አዳዲስ ነገሮችን ተማረች። እጽዋትንና አስተዳደጋቸውን ተማረች። ራሷ እንዴት እንዳደገችም አስታወሰች። በሚያማምሩት የኬንያ ደኖች ከወንድሞቿ ጋር የተለያዩ ጨዋታዎችን ስትጫወት ነበር ያደገችው።



ብዙ እየተማረች ስትሄድም የኬንያን ህዝብ መውደዷ የበለጠ እየተገለጠላት መጣ። ደስተኛና ነጻ ሕዝብ እንዲሆን ፈለገች። ብዙ እየተማረች ስትሄድም የአፍሪካው ቤቷ ይበልጥ ትዝ እያላት መጣ።





ትምህርቷን ስትጨርስ ወደ ኬንያ ተመለሰች። አገሯን ግን ተቀይራ አገኘቻት። ትላልቅ እርሻዎች አገሪቱን አጥለቅልቀዋታል። ሴቶች ለማገዶ የሚሆን እንጨት አልነበራቸውም። ህዝቡ ደህይቶ ልጆቹ ተርበዋል።